በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የመ.ቁ.238487

ጥቅምት 02/2016 ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች፡ 1. አቶ እንግዳሸት ቡናሬ ሁንዴ

2. አቶ ጌቱ ቡናሬ ሁንዴ — **ጠበቃ አቶ አገኘሁ አምባቸው ቀርበዋል አመልካቾች ጋር**

3. ወ/ሮ በላይነሽ ቡናሬ ጀምበሬ

4. ወ/ሮ አሰገደች ቡናሬ ጀምበሬ

ተጠሪዎች፡1. ወ/ሮ ሰላማዊት እሸቱ ቡናሬ — **ጠበቃ አቶ ክብረአብ አበራ ቀርበዋል፡፡**

2. ወ/ሮ ቤተልሄም እሸቱ ቡናሬ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የውርስ ሀብት ክፍፍልን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/288075 ላይ ጥቅምት 21/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

ማሳሰቢያ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የአሁን አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡትን የውርስ ሀብት ክፍፍል ጥያቄ በይርጋ ውድቅ ያደረገበትን ውሳኔ ማጽናቱን በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካቾች መስከረም 04 ቀን 2014 ዓ.ም ፅፈው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁን ተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ጭብጥ ወላጅ አባታቸው የሆኑት ሟች አቶ ቡናሬ ሰኔ 1963 ዓ.ም እንዲሁም ወላጅ እናታቸው ወ/ሮ አስናቀች ሁንዴ ሐምሌ 11 ቀን 1969 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ከተለዩ በኋላ ንብረትነቱ የሚቾች የሆነ እና በአዲስ አበባ ከተማ ልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የቤት ቁጥር 138/139 ተብሎ በሚታወቅ ቤት ውስጥ ሲኖሩ ቆይተው በተለያየ ጊዜ ጋብቻ እየመሰረቱ ከቤቱ ለቀው ሲወጡ በወራሾች ስምምነት ቤቱን ወንድማቸው የሆኑት የአሁን ተጠሪዎች ወላጅ አባት እየኖሩበት ሲያተዳደሩት ቆይተው መጋቢት 2013 ዓ.ም የሞቱ መሆኑን፣ ከዚህ በኋላ የአሁን ተጠሪዎች ራሳቸውን ብቸኛ ወራሽ በማድረግ በሀሰት ማስረጃ ቤቱን ይዘው ያሉ መሆኑን በመግለፅ በፍርድ ኃይል ተገድደው የውርስ ድርሻቸውን እንዲያካፍሏቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪዎች ለዚሁ ክስ በሰጡት መልስ ክስ የቀረበበት ቤት ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ በወላጅ አባታችን ስም ተመዝግቦ የሚገኝ እና ብቻቸውንም ሲጠቀሙበት የቆዩ ነው፣ ሟች አቶ ቡናሬ ከሞቱበት ከ1963 ዓ.ም ጀምሮ በቤቱ ላይ የቀረበ ጥያቄ ሳይኖር ከ50 ዓመታት በኋላ የክፍፍል ጥያቄ መቅረቡ ከህግ አግባብ ውጭ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ/1000(2) እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 244(ሠ) መሰረት ክሱ በይርጋ ይታገዳል፣ ንብረቱም በአባታችን ስም ተምዝግቦ የሚገኝ በመሆኑ በቤቱ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት እና ጥቅም የላቸውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያው ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ እና የቤቱንም ማህደር አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ የአሁን ተጠሪዎች አባት በወራሾች ስምምነት ክስ በቀረበበት ቤት ውስጥ ሲኖሩ የነበረ ለመሆኑ የሚያረጋግጥ የቀረበ ማስረጃ የለም፣ የቤቱ ስም ሀብትም ቢሆን ከመጀመሪያው ጀምሮ በተጠሪዎች አባት ስም የነበረ ስለመሆኑ የቤቱ ማህዳር ያስተረዳል፣ አመልካቾችም ክስ ያቀረቡት ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት በተጠሪዎች አባት ከተያዘ ከ3 ዓመት በኋላ እንዲሁም ሟቾች ከሞቱ ከ15 ዓመት በኋላ በመሆኑ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1000/1/ እና /2/ እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥት 244/ሠ/ መሰረት በይርጋ ይታገዳል በማለት ሁለተኛውን መቃወሚያ መመርመር ሳያስፈልገው አልፎ ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡

አመልካቾች ይህንኑ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካቾች ክስ ያቀረቡት የውርስ ሀብት ለመካፈል በሚል ሲሆን ወራሽነታቸውን ያቀረጋገጡት በ2013 ዓ.ም መሆኑን ያቀረቡት ሰነድ ያሳያል፣ የወራሽነት ጥያቄውም ሆኖ ክፍፍሉ የተጠየቀው አውራሾቻቸው ከመሆኑ ከ49 ዓመት በኋላ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በምክንያት በማጠናከር አጽንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች ታህሳስ 06/2015 በተፃፉ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካቾች የውርስ ሃብቱን በጋራ ሲጠቀሙበት የነበረ ስለመሆኑ በጠቀሱት ሁኔታ የቆጠሯቸውን እና እንዲቀርቡላቸው የጠየቋቸው ማስረጃዎች ሳይሰሙ የክስ አቤቱታው በይርጋ ይታገዳል የመባሉ አግባብነት በዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

ማ ሲታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገበዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንግዲህ ከክርክሩ አመጣጥ መገንዘብ እንደተቻለው አመልካቾች ክስ ያቀረቡት በወራሾች ስምምነት መሰረት በአሁን ተጠሪዎች አባት እጅ እንዲቆይ የተደረገን የወላጆቻቸውን የውርስ ሀብት ለመካፈል ነው፡፡ የውርስ ሃብት ክፍፍል ጥያቄ የሚነሳው ስለወራሾችም ሆነ የውርስ ንብረት ቀድሞ ተጣርቶ እና ተለይቶ በታወቀበት ሁኔታ ውስጥ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1062 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ መልኩ ቀድሞ ተለይቶ የታወቀ ነገር በሌለበት ስለውርስ ሀብት ክፍፍል ጥያቄ ሊነሳ አይችልም፡፡ የውርስ ሀብት ክፍፍል ጥያቄ በይርጋ አይታገድም የተባለውም ስለወራሾችም ሆነ ስለውርስ ሃብቱ ምንነት በህግ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ቀድሞ ተለይቶ የታወቀ በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ የውርስ ሀብት ክፍፍልን የሚመለከት ቢሆንም በራሳቸው ወራሽነታቸውን ያቀረጋገጡት በ2013 ዓ.ም ውስጥ መሆኑን የስር ፍርድ ቤቶች ያቀረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ አመልካቾችም ቢሆን በዚህ መልኩ ክሱን ከማቅረባቸው ውጭ ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት የውርስ ሀብት መሆኑን እና እራሳቸውም ወራሾች ስለመሆናቸው ቀድሞ ስለመረጋገጡ የሚያሳይ አስረጂ ያላቀረቡ መሆኑን ፍርድ ቤቶቹ ገልፀዋል፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1062 ተጠቅሶ አቤተታው በይርጋ አይታገድም የሚባልበት ህጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/288075 ላይ ጥቅምት 21/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻላሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ተ

ማ ሲታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም